የረቡዕ መስከረም 25 1998 ዓም( ኦክቶበር 5 2005)

# የፍኖተ ዴሞክራሲ

## ሐተታ

### የዛሬው ሕዝዊ አመፅ

### የነገ ዴሞክራሲ ዋዜማ ነው።

*ከመከራውና ከጨለማው ዋሻ መዝለቂያ የሚታየውን የብርሃን ውጋገን ወደ ሙሉ ነፃነት ፋና ለመለወጥ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሞት-ሽረት ትግል በማድረግ ላይ ይገኛል። የተጫነበትን ቀንበርም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከጫንቃው አሽቀንጥሮ ለመጣል የአንድነትና የኅብረት ኃይሉን አጥንክሮ በመታገል፥ ማንነቱን ለዓለም በማሳየት ላይ ይገኛል። ቁርጥና ፈታኝ ወቅት ሲመጣ፥ ምን ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደር-የለሽ አንድነትና ኅብረት ማሳየቱ በታሪክ አጋጣሚዎች ሁሉ የታየ-የተረጋገጠ ነው። በአንፃሩ ደግሞ የጋራ ጠላቱ፥ ይህን ኅብረትና ኃይል ሲያይ፥ ብርክ እንደሚይዘውና በመጨረሻም ዶጋመድ ሆኖ እንደሚተን ማንም ሊጠራጠር አይችልም። ይህም ክስተት፥ በታሪክ ተደጋግሞ ታይቷል።*

*በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያለውን የፖለቲካ መልክአ-ምድር በቅርብ የሚከታተል ማንኛወም ታዛቢ፥ ከላይ የተነገረውን ሀቅ ሊገነዘብ ይችላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሔረሰብ፤ በሃይማኖት፥ በመደብ፥ በጾታና በሌላውም ሰው-ሰራሽ ልዩነት ሳይከፋፈል ዛሬ በኅብረት ትግሉ ዘረኛውን ሥርዓት አሽቀንጥሮ ለመጣል ቆርጦ ተነስቷል። የታሪክ ንጽጽርን ማስገንዘብ ካስፈለገ፥ በ1996 ዓም ከየካቲት እስከ ግንቦት የነበረው የሕዝባዊ አመፅ ሂደትና፥ ከግንቦት 1997 ዓም አንስቶ እስከ አሁን ወር ድረስ በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ ሰላማዊ ትግል፥ በብዙ መልኩ ተመሳሳይነት አለው ብንል፥ ከዕውነት የራቀ ነው ሊባል አይችልም። ታዲያ ይህንን የታሪክ ግንዛቤ፥ በዕይታችን አድማስ ማስገባት ከቻልን፥ ዛሬም እንደ 66ቱ የካቲት ሕዝባዊ አመፅ ሁሉ፥ ሕዝቡ በዘረኛው ሥርዓት ላይ አምፆ ተነስቷል። ገዥው ፓርቲ እንደአለፉት አስራ አራት ዓመታት ሁሉ እንደልቡ መግዛት አልቻለም። በብዙው የሀገሪቱ መስተዳድሮች የተመደቡት የወያኔ አገልጋዮች ሕዝቡን በመፍራት፥ የፖሊስ ኃይል ወደሚገኙባቸው አካባቢዎች በመሸሽ ላይ ይገኛሉ። የፀጥታውና ሌሎቹም የመጨቆኛ መሳሪያዎች ለጊዜው መለስ ዜናዊ ታዛዦቸ ናቸው ብሎ እራሱን ቢያታልልም፥ ነግ- ከነከወዲያ ከወገናቸው፥ ካበላቸው ካስታጠቃቸውና ካሰለጠናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን፤ከትግሉ ጎን*

*እንደሚወግኑ መጠራጠር አይቻልም፡፡ ለጊዜው  ሕዝብ እያሰቃዩ፥ እየገደሉና መዳረሻውን እያጠፉት እንደሚገኙ ግን ሊሳት አይገባውም፡፡*

*የዓለም አቀፉ፥ የአህጉራዊውና የአካባቢው ሁኔታዎችም፥ የዴሞክራሲ እንቅስቀሴዎችን ክስተት የሚያራምዱ እንጅ ለአምባገነን ሥርዓት የሚሆን ወቅት የሚጋብዙ አልሆኑም፡፡ የሀገራችን የኢኮኖሚ ሁኔታም በየዕለቱ፥ እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ ነው፡፡ የሥራ አጡ ቁጥር የትየለሌ እየሆነ መጥቷል፡፡ የሥርዓቱ ደጋፊዎችና ተባባሪዎች እንዲሁም መለስ ዜናዊና የቅርብ ግብረ አበሮች የሀገሪቱን ኃብት በገፍ ወደውጭ በማሸሽ ላይ ናቸው፡፡ ኢሕአዴግ ብሎ እራሱን የሚጠራው ድርጅትና መዋቅሩ እየተፍረከረክ እንጅ ጥንካሬንና የሕዝብን አመፅ መቋቋም የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ፥ መለስ ዜናዊ እራሱ ያወጣውን ህግ እራሱ ማዋረድና መጣስ ባልተገደደም ነበር፡፡ የዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲም የተፈጥሮው ባኅርይ በመሆኑ፥ የሕዝቡን አመፅና ጥንካሪ እየተገነዘበ በመጣ ቁጥር፥ በመለስ ዜናዊ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ ብቻ ሳይሆን፥ጊዜን ጠብቆ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፊቱን እንደሚያዞርበት ታሪካዊ ሀቁ ያስረዳል፡፡  በፃዕረ- ሞት ላይ ያለውን ሥርዓት ወደከርሰ-መቃብሩ ለመክተት ግን የመጨረሻው ዋስትና የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ብቻ  መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ግዳጅን ሆነ ድልን ለሌላ አሳልፎ አይሰጡምና ነው፡፡*

*ይህንን ዕውን ለማድረግ ግን፥  የሰሞኑን የፖለቲካ ዕውነታና ሂደት፥ ማለትም፥ የሕዝቡ አመፅ  የደረሰበትን ደረጃ፥ የመለስ ዜናዊን የሚይዘው የሚጨብጠው የማጣቱ ጉዳይና በኢትዮጵያ የሚገኙት የውጭ ሀገር አምባሰደሮች የሚያደርጉትን ጎጂ ጣልቃ ገብነትና የመለስ ዜናዊን ፃዕረ ሞት እስትንፋስ ለመስጠት የሚባክኑትን፤  የሚርገበገቡትን ጭንቀት በሚገባ ማስተዋልና ተገቢውን የትግል አቅጣጫ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነትና ተግባር ለመፈፀም ደግሞ ፥ ሀገራዊ ቀምበር የተጣለበት የተቃዋሚው ጎራ ነው፡፡ የተቃዋሚው ጎራ፥ የአመራር ችሎታው፥ ለሕዝብ ታማኝነቱ፥ የሞራልና የሰብዕና ጥንካሬው፥ የራዕይ ግልፅነቱ፥ የብሔራዊ አጀንዳው ተቀባይነቱና የኅብረት አንድነቱ ወሳኝ መሆኑን አስቀድሞ መገንዝብ አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ለማየት ሁል ጊዜ እንደጓጓ ነው፡፡ ሁሉም ተሟልቶ አይቶታል ለማለት ደግሞ የሚቻል አልሆነም፡፡ ሕዝቡና ተቃዋሚው ጎራ በአንድ ዓይነት ዕመምና አቅጣጫ አይደሉም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ወያኔን ከሥልጣን እንዳወረደው በግንቦቱ ምርጫ በማያሻማ መንገድ ወስኗል፡፡ የተቃዋሚውንም ጎራ ግልፅ በሆነ ቋንቋ ውሳኔውን እንዲያስፈፅም ነግሮታል፡፡ የተቃዋሚው ጎራ ግን እስካሁን ድረስ የሕዝቡን ውሳኔ በተግባር ለመተርጎም አልተቻለውም፡፡ ለሕዝብ ያለውን የማያጠራጥር ታማኝነት ለመግለፅም ፈተናውን የአለፈ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የመንፈስም ይሁን የተግባር፥ የራዕይም ይሁን የትግል ታክቲክና ዕቅድ/ስትራተጂ አንድነት ቀርቶ ተመሳሳይነት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡ የቅርብም ይሁን የሩቅ ተመሳሳይ የትግል አጀንዳም አለመኖሩ፥ ይኸው አሁን የአለንበት ሁኔታ ህያው ምስክር*

ሆኗል። የሰሞኑ የሀገራችን ሁኔታ የሚከተሉትን ተጨባጭ ዕውነታዎች እንድንገነዘብ አድርጎናል።

1) የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦቱ እንቅስቃሴው የጀመረውን ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ለመድገም፥ እንደገና በመስከረም 22/ 98 ሙሉ ዝግጅት ቢያደርግም፥ በወያኔ መሪዎች ተከለከለ። ሰብዓዊና የዜግነት መብትንም ተገፈፈ። ከአገዛዙ ፈቃድ ውጭ ሰለማዊ ሰልፍ ማድረግ ሲቻል፥ ኃላፊነትን ባለመፈልግ ሰልፉ እንዲሰረዝ ሆነ።

2) የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችም እነርሱ ብቻ በሚያውቁት ምክንያት ሰላማዊ ሰልፉ ተሰርዟል የሚል መግለጫ አወጡ። ሕዝቡ ከላይ እስከ ታች አዘነ። ተበሳጨ። አንጀቱ ተቃጠለ። ወያኔና ደጋፊዎቹ ግን ጮቤ ረገጡ። ጊዚያዊ እፎይታንም አገኙ። መለስም ጨልሞበት ከነበረው ሁኔታ ዳፍንት ያህልም ብትሆን ብልጭ አለችለት።

3) ይህ የሕዝቡ ቁጣ ያስደነገጣቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ እንደገና ሌላ ውሳኔ፥ ማለትም፥ በሰላማዊ ሰልፉ ፈንታ፥ ሕዝቡ ከሰኞ ጀምሮ እስከ ረቡዕ ድረስ በየቤቱ እንዲቀመጥና ተቃውሞውንና ቁርጠኝነቱን እንዲገልፅ ጠሩ። አሁንም ሕዝቡ ተባባሪነቱን ገለፀ። ለዚህም ዝግጅቱን ቀጠለ። ይግረምህ ተብሎ ግን፤ አሁንም ይህን ውሳኔ በተግባር እንዳያውል በዚያው ምሽት ሌላ መግለጫ ተሰጠው። የተሰጠውም ምክንያት፥ በአዲስ አበባ የሚቀመጡ የውጭ አምባሳደሮች ጣልቃ በመግባታቸውና ተቃዋሚውንና መለስ ዜናዊን ስለአደራደሩ ነው የሚል ነበር። አሁንም የሕዝቡ ቁጣና ሀዘን ድርብ ድርብርብ ሆነበት። በአውላላ ሜዳ ተጣለ፤ ሀዘን፥ ውርደትና ጥቃትን ተከናነበ። ውጭ ወጥተህ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግም ሆነ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ አትችልም ተባለ። ከሁሉ በላይ ግን አሳዛኝ የሆነው የሕዝብ ድምፅ ኢምንት ሆኖ፥ የባዕዳን ተግሳፅ ሲከበርና ለመለስ ዜናዊ የሚጠቅመው አለህፍረት በሥራ ሲውል ነበር።

4) ባዕዳን፥ ታማኝ አገልጋያቸውን መለስን፥ ከሕዝባዊ ውሳኔና ፍርድ ለማዳን ጣልቃ መግባታቸው ብቻ ሳይሆን፥ በኢትዮጵያና በሕዝቧ የውስጥ ጉዳይ በመግባት ታሪክ የማይረሳው በደል ፈፀሙ። በኢትዮጵያውያን ንፁህ ደም፥ እንዲሁም፥ በስንት ሕፃናትና አረጋውያን የኃጎለ ደም በተቀባው በመለስ ዜናዊ እጅ ለመታበስ መረጡ። ለወደፊቱ ዘላቂ ወዳጅ ሊሆናቸው የሚችለውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ በእጅጉ አሳዘኑ።

5) ኢትዮጵያና ሕዝቧም ዕጓለ ምውታን መሆናቸው በድጋሜ መታወቅ ተቻለ። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የሚረዳውና አሁን ከገባበት የውርደት አዘቅት ሊያወጣው የሚችል ወትሮም አልነበረ። አሁንም የለም። ከራሱ ህብረትና የተፋፋመ ትግል ውጪ ወደፊትም ማንም እንዳማይኖር ሕዝቡ በሚገባ አረጋግጧል።

6) በዕርግጥ መለሰ ዜናዊ በሕዝቡ ቁጣና አልገዛም ባይነት፥ እንዲሁም፥ይህ የማያቋርጥ ሕዝባዊ ትግል የሚያመጣውን ውጤት በደንብ ስለሚረዳ ተርበትብቷል። ደክሟልም። ሀገሪቱንም እንዳለፈው ጊዜ እንደገል ቀጥቅጨ እንደሰም አቅልጨ እገዛለሁ የሚለው ህልሙ የጧት ጤዛ ሆኖበታል። ባጭሩ፥ መለስ እንደመሪ፥ ኢሕአደግ እንደገዥ ፓርቲ ሆነው ሊቆዩ የሚችሉበት እህል ውሃ ተሟጥጧል። የአጋዜ ነፍሰ ገዳይ ቡድንም ሆነ የደህንነት ሰራተኛ መንጋ፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔና ቁጣ ዘወትር ሊያድኑት አይችሉም።

ታዲያ፥ በመጠኑም ቢሆን ከላይ የተዘረዘሩትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ከተገነዘብን ዘንዳ፥ ምን መደረግ አለበት? የሚለውን ጥያቄ ጠይቀን፥ መሆን የሚገባውን አማራጭ መፈለግ አለብን ብለን ማስተላለፍ እንሻለን። በመሆኑም:-

1) የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከዘረኞች ሥርዓት ነፃ መውጣት ከፈለገ አሁን የጀመረውን ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ፥ አጠንክሮና አስፍቶ ባልተቋረጠ መልኩ መቀጠል አለበት። ሕዝባዊ አመፅን የሚገታውና የሚያሸንፈው ኃይል አይኖርም። በተለይ በዕውቀትና በተራቀቀ ዘዴ ከተካሄደ።

2) የተቃዋሚ ድርጅቶች ሚናቸውን የመለየቱ ሁኔታ አፍጥጦ አግጥጦ መጥቶባቸዋል። በወያኔ ፓርለማ የሚገባው ገብቶ፥ የማይገባው አንድ ላይ በመሆን እንደገና አዲስ የትግል ዘዴና ስልት በመንደፍ፥ የሕዝቡን ትግል መምራት አለበት። ወደ ወያኔ ፓርላማ ለመግባት ያቆበቆቡ እንዳሉና ከመለስ ጫማ ስርም ወድቀው ሕዝብን ሊያሳዝኑ የተዘጋጁ መኖራቸው ዛሬ የሚደበቅ ጉዳይ ሰላልሆነ ካልታረሙና ካልታቀቡም ሕዝብ አንቅሮ የሚተፋቸው ይሆናሉ።

3) የባዕዳን ኃይሎች፥ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ የመለስን ቡድን በመደገፍ፥ ኢትዮጵያን የማጥፋቱን ተግባር ማቆም እንዳለባቸው በአጽንኦት ሊነገራቸው ይገባል።

4) የትግሉ ሂደት እየቀጠለ እያለ፥ ውይይቱ መካሄድ ይኖርበታል እንጅ፥ የሕዝቡን ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ እርግፍ አድርጎ በመተው፥ በውይይት ላይ ብቻ ማተኮር፥ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። የትግል ቀመር መሆን ያለበት፥ ውይይት ትግል- ትግል ውይይት እንጅ፥ ትግል አቁመህ ከመለስ ጋር ተወያይ የሚለው አጓጉል ፈሊጥ፥ ትጥቅ አስፈች ብቻ ሳይሆን፥ ለእነመለስ ዜናዊ መሰሪ ተንኮል ሰለባ የሚያደርግ ነው። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ተብሎ አይገመትም።

ይህን ሁሉ አገናዝቦና አዋኅዶ አዲስ የትግል ታክቲክና ስልት ነድፎ የሕዝቡን ትግል መምራትና ከግብ ማድረስ፥ ኢትዮጵያን አጥፍቶ ከሚጠፋ የመለስ ዜናዊ ቡድን፥ ሀገርን ማዳን ይቻላል፡ በአቸናፊነትም መወጣት ይቻላል። ተቃዋሚ ኃይሎች አለምንም ቅድመ ሁኔታ መደራደር ያሉት፥ ከሀቅ የራቀ

ከመሆኑ ሌላ፥ ስህተትም ነው። እነሱ ለእሺ ባይነት ቸኩለው፥ በቅድመ ሁኔታ ደረጃ፥ እስረኞች ይፈቱ እንኳን መጠየቅን ትተው ፥ መለስ ዜናዊ የቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ እናት የሆነችውን የሥራ ማቆም አድማውን ሰርዙና እንደራደር ያለቸው አሳፋሪ ጥያቄ ተፈፃሚነትን አግኝቷል። የሥራ ማቆሙ አድማ ተካሂዶና የሕዝብም ኃይልና የአገዛዙም ልክ ታይቶ በነበረ፥ በፈረጠመ ጉልበት፥ ተቃዋሚ ኃይሎች ቅድመ ሁኔታን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን፥ ማስፈፀምም በቻሉ ነበር። አገዛዙ ለአመፅ ተነሳችሁ ሲል ሰለማዊ ትግላችንን በአመፅ መተርጎሙ ያንት ችግር ነው ብሎና በሰልፉም፥ በሥራ ማቆም አደማውም መቀጠል ሲገባ፥ ይህንን ትግል ማቆሙ ጥይት አልባ ጠመንጃ ይዞ መትረየሰ የሚተኩስን ጠላት መጋፈጥ ዓይነት ሆኗል። በፖለቲካው ዓለም ድርጅቶችና የድርጅት መሪዎች ጉልበታቸው ዝሎ በቃን በዚህ ማለት ቢከጅሉ፥ ይህ መብታቸው ሊሆን ቢችልም፥ የሕዝብን ትግል ግን እያደናቀፉ ከሆነ፥ ስህተታቸው በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። ደክመውና ተከፋፍለው፤ አለምንም ቅድመ ሁኔታ፤ ትላንት የታሰሩትንና የተገደሉትን ደጋፊዎቻቸውን ረስተው፤ ዘላቂውን ጥቅም፥ በውሱን የራሳቸው የድርጅት ችግር ለውጠው፤ ከሕዝብ ተነጥለው፥ ከአውሬው ቤተመንግስት ሊደራደሩ ሲገቡ፥ በእርግጥም አያ ጅቦው ቢያሽካካባቸው--ቢደነፋባቸው የሚጠበቅ እንጂ፥ የሚያስገርም አይሆንም። ለዚህም ነው፥ መለስም ሆነ የአገዛዙ ምላስ ወዲያውኑ ተቃዋሚ ኃይሎች ፈርተውን ተንበረከኩ፤ ስለ ፓርላማ መግባት እንጂ ሌላ አናወያያቸውም ወዘተ ብለው የተሳለቁት።

የሕዝብ ትግልና ፅናት እንዳለ ሆኖ፥ የደረስንበት ወቅት አሳሳቢ ነው። አገዛዙ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ህብረት መዳካም፤ ቁርጠኝነት ማጣትና--መነገር አለበትናም--ፍርሀት በመጠቀም ትግሉን ለማፈን አመቺ ጊዜ አገኘሁ ብሎ እየተንቀሳቀሰ ነው። ተቃዋሚ ኃይሎች አብረውና ተቀናጅተው የሚሰሩ ሳይሆኑ፥ ተወደደም ተጠላም የተወሰኑት የመለስ ዜናዊን ዕቅድ የሚያግዙ ሆነዋል። የሕዝቡንም ውሳኔ ጥሰው፥ በወያኔ ፓርላማ ሊኮለኮሉና መሳቂያ መሳለቂያ ሊሆኑ--በዚያውም እንደ ተቃዋሚ የፖለቲካ ህይወታቸውን ሊያጠፉ--የተነሱ አሉ። ሕዝብ ለወሳኝ ትግል አቆብቁቦ፥ ግን በማስተባበር በኩል ድክመቱን የሚቀርፍለት ኃይል፤ድርጅት ወይም ስብስብ አላገኘም።ያለንበት ሁኔታ ይህ ሲሆን፥ የሕዝብ ጎራ ጠንከር ፈርጠም ብሎ እንዳይወጣ ደግሞ፥ ባለ አቅማቸው የሚሯሯጡ ባዕዳን አሉ። በዚህ ሁኔታ ምን ማድረግ አለብን? ሁኔታው በመጪው ቀናቶች ይብልጥ ግልፅ የሚሆን ቢሆንም፤ በመስከረም 30፥ ማን ፓርላማ ገብቶ ራሱንም ታሪኩንም ሊያዋርድ እንደተነሳ ማየት እንችላለን።፥ ከወዲሁ ግን ሕዘባችንና ህቀኛ ታጋይ ልጆቹ መውሰድ ያለባቸውን ሁለገብ እርምጃ መጠቆሙ ዋጋ ይኖረዋል።

1/ ከወጪ ቀሪ እንዲሉ በእጅ መስጠቱ ጎዳና አልጓዝ ያሉት ድርጅቶች ተሰባስበውና ተባብረው ትግሉን ማስቀጠል መቻል አለባቸው።

2/ የሕዝብ ድርጅቶች፥ ማለትም የሙያና የሲቪክ ማህበራት ጋር የቅርብ ትስስርን አድርጎ ከሕዝብ መያያዝ መቆላለፍ ያስፈልጋል።

3/ በህቡዕ የሚሰራውም በሚሰሩት ተጠናክሮ ሀገር አቀፉ መረብ መዘርጋትና መጠናከር አለበት::

4/ ዳግም የሥራ ማቆምና የሙት ከተማ  አድማ ተጠርቶ በተግባር መታየት አለበት::

5/ የትግሉ ዓላማም ግልፅ መሆን አለበት:: አንድ የተቃዋሚ ድርጅት መሪ እንዳለው÷ ትግሉ መካሄድ የለበት÷ አገዛዙ ቅድመ ሁኔታ ሳይጫንበት ወይም ሳይጭን ለድርድር እንዲቀርብ ሳይሆን÷ የሕዝብን ድምፅና ውሳኔ እንዲቀበል ለማድረግ ነው::

6/ የመለስ አገዛዝ÷ ጉልበቱና ስልቱ÷ ያው አፈና ማካሄደ ነውና÷ ይህንን በሚገባ ለመቋቋም ተመክሮን መሠረት አድርጎ በስልት መዘጋጀትም የግድ ይሆናል::

7/ ለባዕዳንም÷ ይችን ኩሩ ሀገር÷ በሉዓላዊነት የሚገዛት ሕዝቧ እንጂ÷ የከሀዲዎች መንጋ ወይም ማንም ባዕድ አለመሆኑን ደግሞ በተፋፋመና ብርክ በሚያስይዝ ቆራጥ ትግል ልናሳያቸው ይገባል ማለት ነው::

8/ በወሳኝ የትግል ወቅት ፈሪ ተለይ! የሚል ነጋሪትን መጎሰም፤ የአገዛዙ ሰላዮችንና ሰርጎ ገቦች ማስወገድና ጠላት ወዳጅ ላይሆን÷ ለፈስፈስ--ለስለስ የሚሉትንም ከወሳኝ ቦታዎች አርቆ ለመጨረሻው ድል መዋደቅ ያስፈልጋል::

9/ ይህን ታሪካዊ ትግልም÷ በባዕድ ሀገሮች ያሉ ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ድርሻቸውን ሊወጡ ይጠበቃል::

የሀገርና የሕዝብ የነገ ዕጣ÷ የህልውና ጉዳይ ነውና÷ በዝምታና በይሉኝታ የምናልፈው ክህደት ወይም ከባድ ስህተት ሊኖር አይቸልም፤ አይገባምም:: በሕዝብ ትግል ላይ ጉዳት ያመጣ ወደደም ጠላም ለአገዛዙ ይጠቅማል:: ከሁለቱም መሆን ደግሞ አይቻልም:: ስለዚህም ሀቀኛውን የሕዝብ ወገን ከአስመሳዩ መለየትና ሰማይ ከመሬት ቢገጥም መለስና ጭፍሮቹ ከአጋንንት ጠባያቸውና ፀረ ሕዝብነታቸው መቸም ሊቀየሩ እንደማይችሉ ማወቅ ደግሞ የግድ ነው::

የመለስን አገዛዝ ለማንብርከክ የተጀመረው ሕዝባዊ ትግል ይፋፋም!!
ለቁርጠኛ ትግል እንዘጋጅ!!